ነሐሴ 25 ቀን 2003 ዓ.ም

# ቸገረን እኮ!
# በአፍ ይጠፉ፤ በለፈለፉ!።

ከ አያልነሽ

ፖለቲካችን እንዴት ሠንበተ ብዬ ፖለቲካችንን ልዳሥስ እነሆ ዛሬ ብቅ አልኩ። አምላክ ይመስገን ፓለቲካችንም አላሳጣኝም፤ የሚተች፣ የሚፈተሽ ነገር አልጠፋውምና የኃሳብ ነፃነቴን ተጠቅሜ የምለው ቢኖረኝ፣ ለመፈተሽ ፈቀድኩ። እንደእኔ እንደእኔ ከሆነ ለፖለቲካችን፣ **ትችት** ፍቱን መድኃኒት መሆኑን ያኔ ሚጢጢ እያለሁ ያ "**አክራሪው**" ኢሕአፓ በቦጅቦጅ እየጠቀለለ አጉርሶኛል፤ በወንዞቻችን ውኃ እያዋዛም ግቶኛል። እናም ማንኛውም ትችት ለእኔ የመድኃኒት ያህል ፍቱን ነው ብዬ የማምን ሰው ነኝ ። ስለሆነም ፖለቲካችን እንዲሾርና መልክ እንዲይዝ ከፈለግን ደግሞ ትችትን ማበረታት እንጅ፥ "**እንኳንስ ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ**" ዓይነት በሰበብ አስባቡ ጥቂት ተችዎች ቢኖሩም እነኛን ጥግ ለማስያዝ ከፍና ዝቅ ማድረግ፣ የትም የማያደርስና ከዴሞክራሲ ጋር የተጣላ አካሄድ ነው ብዬ አምናለሁ።

ልብ በሉ! በአምባገነኖች አገዛዝ ሥር ስንታሽ የኖርንና አሁንም እየታሸን ያለን ዜጎች መሆናችን አይዘነጋም። እና ገና ለገና በስመ ተቃዋሚ "**ተቃውሚ ነን በሚሉ ኃይሎቻችን**" ደግሞ ትችትን ስድብ ነው እያሉ ተችዎችን አፍ ለማስያዝና ለማሸማቀቅ ሩቅ መንገድ መጓዝ፣ ጨርሶ ኃላፊነት የጎደለው በመሆኑ ቶሽ ሊባል ይገባል። መወደስ/መደነቅን ብቻ የሚፈልግ ግለሰብ፣ አመራር፣ መሪ ወይንም ቡድን ካለ፣ የነገ ጉዞው አምባገነንነት መሆኑ አይቀሬ ነውና ከወዲሁ እኛ- ደግሞ አምባገነንነትን እየኮተኮትን ውኃ እንድናጠጣ ፈፅሞ አይጠበቅብንም። የትግላችን አልፋ ኦሜጋና ትግላችንም እልህ አስጨራሽ የሚሆንበት ዋና ምክንያትም የዛሬውን አምባገነን ከመጣል ባሻገር ፣ ነገ የምንተካው ሥርዓትም ፍጹም ዴሞክራሲያው አስተደደር ይሆን ዘንድ መሠረቱን ለመጣል ጭምር ነው። የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር የመሠረት ድንጋይ ደግሞ፣ እንደ እኔ ዕይታ፣ ትናንትም ሆነ ዛሬ ዜጎች ሳይሸማቀቁ ሃሳባቸውን በነፃ ማንሸራሸራ መቻላቸው ነው። አለበለዚያማ ያሰበ ወይም ያሳሰበ ዓይነት ጥሩምባ ትርፉ፥

**ትችት በቁጠባ - ኃሳብ በቁጠባ፣**
**ሁሉኑም ጠራርጎ ይዞ ገደል ገባ።**

እንዳይሆን መጠንቀቅ ይኖርብናል። የመንግሥቱን፣ የቤን አሊን፣ የሙባረክን፣ የጋዳፊን እና ነገም የዜናዊን እጣ ፋንታ ለተመለከተ፣ አቶ ትችትን **ጎሽ፣ ዕደግ ተመንደግ ልንለው** ይገባል። ዱባና ቅል አበቃቀላቸው ለየቅል ነው። ስድብና ትችትም እንዲሁ ፈፅሞ በይዘታቸው የተለያዩ መሆናቸውና ለየቅል መሆናቸውን ለታዛቢ እነግራለሁ ብሎ መድፈር፣ ብዙኃኑን ታዛቢ የመናቅ ያህል ይሆንብኛል። የዛሬን አያድርገውና ቀድሞማ ስደብ ለኢትዮጵያኖች የነውር ነውር ነው። አስተዳደግንም ያስፈትሻልና ነው። ስድብ በመሠረቱ ፀያፍ ነው። የሚሳደብም ሰው ራሱን/ራሷን ያስገምት/ታስገምት እንደሆን እንጅ የሚያስገኘው ትርፍ የለም። ስድብን በአዋጅና በአደባባይ መሣርያው አድርጎ ያመጣውና የሚጠቀምበት፣ የስድነት ባላባት የሆነው ወያኔ ነው። ወያኔን ከሥረ መሠረቱ ለምናውቀው ደግሞ ይሄ ስድነቱ እስካሁን ደረስ እንደቀጠለ ያለ ለመሆኑ ዋቢ ማቅረብ አያሻም። ከስብሃት ነጋ ጀምሮ ያሉትን መመልከት ብቻ ነው።

ትችት ግን በመሠረቱ ፈጽሞ የተለየ ነው፤ ገንቢና አስተማሪም ነው። ትችቶች ደግሞ ጠቃሚነታቸው የግድ ለሚተቹት "**ተ**" (ጠበቅ ብሎ ይነበብ) ግለሰቦች ሆነ ለሚተቹት ተቃዋሚ ኃይሎች ብቻ ሳይሆን፣ ትችቱ ለማይመለከተው ብዙኃኑ ሁሉ አስተማሪነቱ አንድና ሁለት አይባልም። ይህ ብቻ አይደለም። ማንም ሰው ሃሳቡን ሆነ ትችቱን በፈለገው መንገድ ለመግለፅ

መቻሉ የተከበረ የግሉ መብት መሆኑን ማወቅ በራሱ አንድ ሥልጣኔ ነው። ለዚህም ነው አፄ ምኒልክ የገበሬን ብሶት ለማዳመጥ ሲሹ፣ "**ገበሬ ምን አለ**" ብለው የህዝብን ብሶት ለማዳመጥ ይጓጉ ነበር የሚባለው።

እነሆ! በዚህ መርህ መሠረት ፖለቲከኞቻችን ሊብጠለጠሉ ማለትም ሊተቹ፣ አርቲስቶቻችን ሊነገሩ፣ ሊጠርቡ ሊተቹ፣ ጋዜጠኞቻችን፣ ወዘተ፣ ወዘተ… ሊፈተሹ፣ ሊገመገሙ፣ሊዳሰሱ ይገባል ማለት ነው። (ከቃላት ስንጠቃው በመለስ ማለት ነው) አለበለዚያ በየመድረኩ ልታይ፣ ልታይ ወይም ልታወቅ፣ ልታወቅ እያሉ ሲተቹ ደግሞ ቡራ ከረዩ ማለት "**ከሥጋው አውጡልኝ ከመረቁ ግን ያመኛ ነኝ**" እንደማለት ይሆናል። ነፃ ፕሬስ ነኝ ማለት ብቻውን ደግሞ በቂ አይደለም። ነፃ ፕሬስ ነኝ በባዶውም፣ በተቃጠለ በረሃ ላይ ጋቢ እንደ መልበስ ነውና ሊሠራ አይችልም። ትችቶች እጅግ አስፈላጊ ናቸው። እንዲህ ዓይነት ትችቶችን ደግሞ ከዚሁ ካልተለማምድናቸው፣ ዳውድ ኢብሳ ፊንፊኔ ሲደርስማ፣ ኃሳብና ትችት በፊርማ ይሆናል ማለት ነው - አይመስልችሁም!? ለስኮንድ አስቡት እስቲ **<u>ኃሳብ እየሳብኩ ነውና ማሥቤን በፊርማዬ አረጋግታላሁ ስንል !</u>** ታየኝ ልክ እንደ ወያኔ ዓይነት። በስመአብ! ይህንን የኢሣያስ ጆሮ አይስማ!።

እሺ! ለመሆኑ <u>ፖለቲካችን ምን ላይ ደረሠ፣…?</u>

በጄ! ጥያቄው ጥሩ ነው። ፖለቲካውና ፖለቲከኞች እየተፋተጉ ነው። መጥፎ አይደለም፤ ከአሁኑ ካላጠሩት በኋላማ አያደርሳቸውም። ጎበዝ! እንደምናየው ዙፋን እኮ ጊዜ አይሠጠምና ነው። "**ሥልጡን**" ፖለቲከኞች እና "**ፋራ**" ፖለቲከኞች በፖለቲካው አውድማ ላይ እስከአሁን መግባባት አልቻሉም፤ ይህ አለመግባባታቸው ደግሞ መሠረት ያለው ነውና የሚጠበቅና የማያስገርም ነው። ቀጣይነትም ሊኖረው ይችላል። ይልቁንም ሁለቱ ፖለቲከኞች በማያግባባቸው ነገር ላይ በተከራከሩ ቁጥር፣ የበለጠ ጥራት ይኖርና ጥርት ያለና ጤነኛ የሆነ ማህበረሰብ ሆነ ሕበረተሰብ ይኖር ዘንድ መሠረት ይጥላሉ ባይ ነኝ። ይህ የኔ የ"**ፋራዋ**" አመለካከት ነው። "**ሥልጡን** "ፖለቲከኞች በዚህም ላይ አይሰማሙም - ችግር የለውም አለማስማማታቸው እንደመስማማቱ ሁሉ መብት ነውና አያስከፋም። እንዲያውም ውይይቱ ይጦፋል፣ ይበራያል፣ ያልጠራው እንዲጠራ ያደርጋል። ህዝብም ጉዳዩ ነውና ይሳተፍበታል ማለት ነው።

ግን አሁንም ቢሆን "**ዘመናዊ ፖለቲከኞች**" ይህንን አባባል አይጋሩትም እንዲያውም ቅሬታ አላቸው። ቅሬታቸው ደግሞ እንዲህ የሚል ነው፥ የምን ጥራትና ውይይት ነው? ውይይት፣ ትችት ምናምን እኮ ጊዜ ሲኖር ነው፤ አሁን ለዚህ ጊዜ የለንምና ያልጠራም ውኃ ቢሆን መጠጣቱ የግድ ነው ይሉናል። ካልሆነማ ውኃ እናጣራ ምናምን ስንል በ6 ወር ቀርቶ በ8 ወርም አዲስ አበባ መግባታችን ያጠራጥራል ይላሉ። ሆ! ሆ! ሆ! ታዲያሳ ምን ተሻለ ስንላቸው ደግሞ በአስተርጓሚ "**አሁን ወያኔን መጣል ነው**" በኋላ ግን አልሸባብ ይሁን አሸብር ፤ ደቻሳ ይሁን ሞሲሳ፤ ትጁቤ ትሁን አብረሀት፣ ብቻ ወያኔ ይውደቅ እንጅ ያኔ እንደገባን በ"**ሪፌረንደማችን**" እናጣራዋልን ብለውን እርፍ! በቃ ተከተተ፣ ያስቃል አይደል። ይገርማል! እኔ ደግሞ ፈርዶብኝ በተፈጥሮዬ ፊልምን አንድ ጊዜ ብቻ ነው ማየት የምወደው ለዛያውም ካልሰለቸኝ ነው። ሃ ! ሃ! ሃ! ሃ!

ድሮ፣ ድሮ ፍቅር በደብዳቤ ሲባል አውቅ ነበር …አሁን፣ አሁን ደግሞ ትግል በአስተርጓሚ ሆነና ሰውን ሁሉ አጃኢብ እያሰኘ ነው። እኛ ምን ገዶን ታዲያ ! ብቻ ተርጓሚም ሆነ አስተርጓሚ ገዝተንም ቢሆን ማዳመጣችንና መደማመጣችችን አይቀርም። እዲህም ሆኖ ትችታችንም የዚያኑ ያህል ይጦፋል፣ያድጋል ማለት ነው። በሽ በሽ ! ዴሞክራሲ!።

የወያኔ ውድቀት በእርግጥም አይቀሬ ነው። ከወያኔ ውድቀት በኋላስ? የሚለው ደግሞ ከአሁኑ የመነጋገሪያ ጉዳያችን ነው። የምንነጋገረው ደግሞ ነገ ሳይሆን ዛሬም ነውና የትችቶቻችን መንፈስም ከዚሁ አንፃር ሊበረታታ ይገባዋል። እንደዜጋም የሃገራችን ጉዳይ በመሆኑ በጣም ያሳስበናልና ነው። ግን በስመ ሰደባችሁን አባዜ ተመሳሳይ ወያኔን ለማምጣት ደፋ ቀና ሲባል እያየን ደግሞ ፍቀዱልን ልንባል ከቶ አይጠበቅም። <u>**በእናት ሃገርና በሚስት የለም ዋዛ**</u> ይባል ነበር በእኛ ጊዜ።....አሁን ግን ይሄ ሁሉ "**የፋራ ጨዋታ**" ነው ተብሏል ቂ ቂ ቂ ቂ!
ፋራዎች ደግሞ የፈለገ ቢባል የያዙትን ይዘው '**እምቢ ያባ ቢለዋ ልጅ**' ብለው ይሞግታሉ - ያው የተለምደ ነው ስሙ **አክራሪነት**! ነው- ቆዩ እስቲ መዝገብ-ቃላትን ልይ። ወይ መዓልቲ አሉ ዮሐንስ ለታ!

<u>**ሌላስ ምን ተባለ...?**</u>

ምን የማይባል አለ ልስማ ላለ ሰው። "**ሥልጡን ወይም የሠለጠነ**" ፖለቲካን ነው የምናራምደው ባዮች ሌላም የሚሉት አላቸው። እንደእነርሱ አባባልና አስተሳሰብ ከሆነ አለመግባባት በራሱ "**ኋላቀርነት ነው**" በማለትም ይፈርጁታል። እናም ይሄ ነውና ትርጉሙ ሌላው ቢቀር ይላሉ ሌላው ቢቀር ካልተግባባን እንኳ ቢያንስ "**አንነካካ**" የሚል ማጠየቂያም ያቀርባሉ። በዚህ አያቆሙም፤ ይህንን አባባላቸውን ያጠናክርላቸውም ዘንድ እንዲህም ሲሉ ይደመጣሉ።

> **ለዛሬው ትግላችን በውነቱ የትናትን ነገር ማጣቃስና ማንሳት ሳይንሳዊ አይደለም ብለው፣ "ዶክተራዊ" ትንተና ያቀርቡና በኃላ ግን መለስ ብለው፣ ከራሳቸው ኃሳብ ጋርም ሲቃረኑ ትመልከታላችሁ። የትናንቱን አታንሱ ብለው ወዲያው ደግሞ ለእነርሱ ሃሣብ የሚስማማ ነው ብለው የሚያምኑበትን ኃረግ አንዱን መዘዘው ከትናትና በፊት በፊት ሄደው "የምንሊክ ጡት ቆረጣ ቅብጥርሶ" በማለት ከወቅቱ ጋር የማይሄድ ታሪክን ሲያጣቅሱ ይሰተዋላሉ። ዛሬ የምናካሄደው ትግል ይሉናል መልሰው እነኝህ "ሥልጡን ፖለቲከኞች"፥ ዛሬ የምናካሂደው ትግል እውነት እውነት እንላችኋለን ነገ ለምናመጣላችሁ ትሩፋት አስተማማኝ ይሆን ዘንድ፣ እባካችሁ በፈጠራችሁ! የትናንቱ ለዛሬው ፋይዳ የለውምና እርሱት ብለው በምኃላ አፋችንን ሊሸብቡት ይሞክራሉ። አልፈው ተርፈውም ላለመነካካት መኃላ እንፈፅም ብለውም ይማጸናሉ፤ እነሱ መንካካታቸውን ያቆሙ ይመስል!**

ግና እኮ ለመሆኑ ይህ "**አንነካካ**" ማለት ምን ማለት ነው? ቃሉን ዝም ብላችሁ ፍርጥ አድርጋችሁ ስታዩት ድፈን ቅል አይሆንባችሁም? እንዲያው ለነገሩ ሌላው ቢቀር በ20 ዓመቱ ጉዟችን እንኳ ያለፍንበትንና እየኖርነው ያለውን የመከራ መዓትና መንገድ እንዴት ነው እርሱት የምንባለው? ይሄ የመከራ መንገዳችንስ የተሠራውና መሐዲሱና አጋፋሪውስ ማን ነበር? ከምር ይሄ ይሄ ሁሉ ቢዳሰስና ቢፈተሽ ታዲያ ምነድን ነው ችግሩ? ነገ መጥፎ ነገር እንዳይደገም፣ ያየነውንና ሕዝባችንንም እያስከፈለ ያለን ተመሣሣይ ችግር እንዳይመጣ፣ ዛሬ ላይ ቆም ብለን ብንፈትሽ ኃጢያቱ ምንደር ነው። ይህስ ምኑ ይሆን ኋላቀርነቱ.? ወገኖቼ! እውነት እውነት እላችኋለሁ ይህን እየፈጩ ጥሬ ጉዞአችንን ኢትዮጵያዊያኖች በሙሉ ማስቆም መቻል አለብን፤ ሃገራችንን የማዳን ግዴታም አለብንና ነው። ይልቁንም ተሞክሮ፣ ተሞክሮ ያልሠራን ነገርና ተደጋግሞ የተሞከረን ነገር አሁንም ለመድገም መነሣት ኃላፊነት የጎደለውና በሃገርና በሕዝብ ላይ መቀለድ ብቻ ሳይሆን ወንጀልም ነው።

አዎ! ስለ ትናነት ማንሳት አያስፈልግም፤ አለማንሳት ቢቻል ኑሮ ደግ ነበር ግን አይቻልማና ነው። ለመሆኑ የትናንትና፣ የዛሬ በሚል እሰጥ አገባ ውስጥ የሚከቱንስ እነማን ናቸው? እንዲህ ዓይነት

ዝብሪት ምንጩ ምንድር ነው? እስከምንስ ያስኬዳል? እስቲ እንዲህ ዓይነት ትርጉም የሌለውና መሬት ላይ የማይቆም ክርክር ከሚያቀነቅኑ ሰዎች ውስጥ ልጠይቅ! "**ዛሬን ነው የምወደው ብሎ**" የትናንትና እናቱን የሚገድል ማነው? የዛሬ ሰው ነኝ ብሎ ቆሞ ለመናገርም፣ የትናንት እናቱ ባትወልደው ኖሮ ስለዛሬ ይናገር ነበር? ትናገር ነበር? ዛሬስ ይኖር ነበር? ስለ ትናንት ሳናነሳ ስለ ዛሬና ነገ ለመነጋገርስ እንዴት ይቻላል?፤ወዘተ፣ ወዘተ.... ብዙ መጠየቅ ይቻላል። ለዛሬውና ስለ ነገ ለምንመኘው መልካም ነገር ከልባችን ከፈቀድን ደግሞ የትናንቱን መርምረን፣ ከትናንቱ በጎውን፣ ከዛሬው ደግሞ አዲሱን ለመወሰድ ያስቻለን ዘንድ ከትናንቱ ስህተታችን ከበጎው የምንማርበትን ለመውሰድ መትጋት እንጅ አታንሱ፣አትነካኩን በማለት "**ኩት አትበሉን የሹም ዶሮ**" መሆን ቦታ የለውም። እንዲያውም ይሄ በዴሞክራሲ ስም ዴሞክራሲን መግደል ነው። በእኛ "**በፋራ ፖለቲከኞች**" ዕይታ ደግሞ ጋት አያራምደም ባዮች ነን።

ሌላም አለ። እነዚህ "***ሥልጡን ፖለቲከኞች***" ነን ባዮች ስለ ዴሞክራሲና ፣ ስለ ሰብዓዊ መብት እየታገልን ነው በማለት ራሳቸውን አባወራ፣ እማወራ አድርገው ራሳቸውንም "**በሽልማት**" ናዳ ሲያጥለቀልቁ እያየን፣ ተመልሰው ግን "**አንነካካ**" በማለት እንዳይተቹ፣ ፋራዎችን ተጨፈኑ እናሞኛችሁ ብለው "**የፋራ**" ጨዋታ ይጫወታሉ።

ሳይንስ የሚለው **ትናንት** ከሌለ፣ **ዛሬ** የሚባል ነገር የለም። **ዛሬ** ከሌለ ደግሞ **ነገ** የሚባል ነገር አይታሰብም። ስለሆነም ከትንናቱ ለዛሬ የምንማርበት እንዳለው ሁሉ፣ የዛሬው ደግሞ ነገ ለምንደርስበት ራዕይ መዳረሻ ሆኖ ያገለግላል ማለት ነው። በቀላል አማርኛ አንድ ባለ መኪና ነድቶ ወደፊት ለመሄድ ከፈለገ፣ በግራ እና ቀኝ፤ እና ከፊቱ ባሉ የመኪና መስታወቶቹ የኋላውን እየቃኘ መንዳት ይጠበቅበታል። ወደፊት ካሰበው ለመደርስ የኋላውንም እየቃኘ መንዳት ግድ ይለዋልና ነው።

እውነት እውነቱን እንነጋገር ካልን፣ ያለፈን ታሪክ ያውም ከዛሬ 100 እና 200 ዓመት በፊት የነበረና ስለ ዴሞክራሲ እንኳ ፅንሰ ኃሳቡ ባልነበረበት ሁኔታ የተፈጠረን የታሪክ ሂደት፣ ለራስ በሚጠቅም መንገድ በማራገብ፤ ብዙ ግፍ ተሠርቶበታል። "**የቡርቃ ዝምታን**" ያስታውሷል። ቀደም ሲል በነበሩት በነኝህ 100-200 ዓመታትም ቢሆን የኢትዮጵያ ህዝብ በገዥዎች ባንድ ላይ እየተረገጠ ነገር ግን በክፉም ሆነ በደጉም እንደሕዝብ አብሮ ተካፍሎና በማህበራዊ ኑሮው ተሳስሮ የኖረ ህዝብ ነው። ይሄንን አሴቱን አሌ ወይም ወደኋላ ገሸሽ በማደረግ፣ አገርና ህዝብ እንዲለያይ ከፍ ባለ ድምፅ ሲያስተጋቡ የነበሩ ሰዎች፣ ዛሬ ስለ ትናንቱና አሁንም ስለምንኖርበት ሁኔታ "**አታንሱ፣ አንነካካ**" ብሎ ሌላውን ለመምከር መነሳት ቢያንስ የሞራል ብቃትን ይጠይቃል። "**የአማራው ህዝብ ከዬት ወደየት**" የሚለውም መፅሐፍ ሌላው ፊታውራሪ ነው/ነበር ።

ይህ መፅሐፍ የተፃፈው በምኒልክ ጊዜ አይደለም። ይህንን መፅሐፍ አፄ ቴዎድሮስ አይደለም የፃፉት። ይህን "**የአማራው ሕዝብ ከየት ወደ የት**" የሚል የመፅሐፍ ታሪክ ተግባራዊ ያደረጉት ጣይቱ አይደሉም፣ ይሄ መሬታችን ላይ ያለ ሃቅ ነው። ግን በዚህ መፅሐፍ ጦስ ስንት ግፍና ስንቱ ኢትዮጵያዊ ከቀዬው እየተመነጠረ ወደ ጉድጓድ መወርወሩን መንገር ደግሞ ለቀባሪው ማርዳት ይሆናል። ይሄ ታዲያ እንዴት ስደብ ሊሆን ይችላል- እውነትና ሐቅ እንጅ። እስከመቼስ ነው እውነትን ሸሽቶ መኖር የሚቻለው..? ይሄ እኮ የትናንትና የ20 ዓመት ጉዟችንና ገናም ያልተገላገልነው ዕዳችን ሆኖ ሳለ ይሄንን እያዬን "**እባብ ያየ በልጥ በረዬ**" ብንሆንስ ምን ያስገርማል?! ደግሞም እኮ የትናንት እባቦቹ ልጥ ነን አሉን እንጅ በእርግጥም ልጥ አለመሆናቸው አፋቸው ሳይሆንም እንቅስቃሴያቸውና እርምጃቸው ጠቋሚ ነው። ስለዚህ ምን አድርጉ ነው የምትሉን ክቡራን ዶክተሮቻችን? እየተስተዋለ እንጅ!

እኛ አንድ አገር ነው ያለችን -ኢትዮጵያ!

የሃገራችን ሕመሟ ደግሞ ያመናል። ቁስሏ ይጠዘጥዘናል። ችግሯ ችግራችን ፤ ረኃቧ ረሃባችን ነው። ጥማቷም ጥማታችን እንጅ፣ ኢትዮጵያ ስትከሳና ስትኮስስ አናውቃትም፣ አፍርባታለሁ እያልን በየአደባባዩ በሃገራችን እና በህዝባችን ላይ አንዘባበትም። ህዝባችን አዎ! በአምባገነኖች ሥር ሲማቅቅ ልጆቹ ነንና፣ የሚያማቅቁትን አምባገነኖች ዛሬም ሆነ ነገ፣ እንደ ትናንትናው ሁሉ ወገባችንን አጥብቀን በፅናት ከመታገል ውጪ ሌላ አማራጭ የለውም ብለን የምናምን ነን። ከህዝባችንም ጋር ቆመን እስከመጨረሻው ድረስ ታግለን አምባገነኖችን እንጥላልን እንጅ አፍረን አንገታችንን ልንደፋ አይቻልንም።

ለእኛ የትግላችን አልፋና ኦሜጋ ሕዝባችን ለሚያደርገው ለዴሞክራሲያዊ መብት ተጋድሎና የሀገሩ ባለቤት ለመሆን ለሚከፍለው መስዋዕትነትም አጋሩ ሆነን አለንልህ ከጎንህ በማለት ትግሉን ዳርቻው ድረስ ለማድረስ ነው። እንጅ የቅንጦትና የገንዘብ መዘረፊያ አድርገን የያዝነው አይደለም። ለእኛ በእያንዳንዷ ቀን በሀገራችን ከአንድ ሰው በላይ ይሞትብናልና ነው። ለእኛ በዳያችን ፈፅሞ አገራችን ኢትዮጵያ አይደለችም፤ የበደሉንና የሚበድሉን - ሡንገው የያዟትና የሚይዟት አምባገነኖችና አገዛዛቸው ነው ብለን የተፈጠምን ነን። ይህን ደግሞ ታገለው የሚገላገሉት አይቀሬ ግዳጅ እንጅ ለነገ የሚለጉት ሐኬት ሊሆን አይችልም። ይህ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያ ኃላፊነትና ግዴታ ነው። ኢትዮጵያ የሁላችንም ናት የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ። ግን ኢትዮጵያዊ አይደለሁም ብሎ የጥቁር ፈረንጅ ለመሆን የሚያመረው ካለ ደግሞ፣ ከበህረ ነጋሹ ንጉሥ ነገሥት ከሡልጣን ኢሳያስ አፈወርቅ(ቂ) መከራ ሊማር ይገባዋል እንላለን-ጨርስኩ።

**የሕዝብ ትግል ያሸንፋል! የታሠሩ የፓለቲካ እሥረኞ በሙሉ ይፈቱ**
**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!**

ቸር ይግጠመን!

ኦገስት 31 /2011